# ለሰብአዊ እርዳታ ለሚውሉ እቃዎችና አገልግሎቶች የታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ***ለሰብአዊ እርዳታ ስለሚውሉ እቃዎችና አገልግሎቶች የታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 23/2001***

በበጐ አድራጐት ድርጅትነት የተመዘገቡና የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ሲያጋጥም በጥሪ ወደ አገር የሚገቡ ድርጅቶች ከውጭ ለሚያስገቡትና አገር ውስጥ ለሚገዟቸው እቃዎች ከታክስ ነፃ የሆኑበትን ሕግ በአግባቡ ማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለሰብአዊ እርዳታ የሚውሉ አቅርቦቶችን የሚገዙ ድርጅቶች የተሰጠውን የታክስ ነፃ መብት ከዓላማው ውጪ ለሆነ ተግባር እንዳይጠቀሙበት ታክሱን ከከፈሉ በኋላ በልዩ ሁኔታ በታክስ ተመላሽ ሥርዓት እንዲስተናገዱ የማድረግ ስልት መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል።

### *1. አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ ***"ለሰብአዊ እርዳታ ስለሚውሉ እቃዎችና አገልግሎቶች የታክስ ነፃ መብት አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 23/2001"*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

### *2. ትርጓሜ*

1) ***"የበጐ አድራጐት ድርጅት"*** ማለት በሰብአዊ አርዳታ፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን የመርዳት ኘሮግራም ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር አቅርበው ተቀባይነት ያገኙና በፍትሕ ሚኒስቴር የእውቅና ሰርተፊኬት የተሰጣቸው እና እንደ ቀይ መስቀል የመሰሉ ተቋማት ናቸው።
2) ***"ታክስ"*** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።
3) ***"ከታክስ ነፃ አቅርቦት"*** ማለት ታክሱ ሳይከፈል የተፈፀመ ግብይት ነው።

4) ***"ደንብ"*** ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 ነው።

5) ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

## *3. የበጎ አድራጎት ድርጅት በታክስ ተመላሽ ሥርዓት ስለሚስተናገድበት ሁኔታ*

የበጎ አድራጎት ድርጅት ለሰብአዊ እርዳታ ወደ አገር የሚያስገባቸውና በአገር ውስጥ የሚገዛቸው እቃዎች በታክስ ተመላሽ ሥርዓት የሚስተናገዱት ድርጅቱ፡-

ሀ/ የውጭ አገር ከሆነ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እውቅና ማግኘቱን የሚያሳይ ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ለ/ አገር በቀል ከሆነ በፍትሕ ሚኒስቴር ወይም በሚመለከተው የክልል መስተዳድር አካል የተመዘገበ፣ የዘመኑ የታደሰ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና ለእርዳታ የተሰማራ መሆኑ ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የተሰጠ ማረጋገጫ ሲያቀርብ፣

ሐ/ ድርጅቱ የእርዳታ ኘሮግራሙን ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና አግባብነት ላላቸው ተቋሞች አቅርቦ ከታክስ ነፃ ወይም በዜሮ መጣኔ የሚስተናገደውን አቅርቦት ዝርዝርና መጠን፣ እንዲሁም የቆይታ ጊዜን የያዘ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን፣

ብቻ ነው።

## *4. ለሰብአዊ እርዳታ ተግባር በቀጥታ ስለሚውሉ ኘሮጀክቶች*

ለሰብአዊ እርዳታና ወይም በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ የተጐዱ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋምና ለመታደግ የሚያስችሉ የመጠለያ፣ የውሃ ቁፋሮ፣ የመስኖ ሥራ የመሳሰሉ ኘሮግራሞች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተቀባይነት አግኝተው የቆይታ ጊዜያቸው ለባለሥልጣኑ ተገልፆ ሲቀርቡ ግብይታቸው በታክስ ተመላሽ ሥርዓት እንዲስተናገዱ ይደረጋል።

## 5. በታክስ ተመላሽ ሥርዓት የማይስተናገዱ

ከሰብአዊ እርዳታ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው እቃዎች፣ የቤት አውቶሞቢሎች፣ የግል መገልገያዎችና ለእርዳታ ሠራተኞች የሚውሉ የፍጆታ እቃዎች በዚህ መመሪያ አይስተናገዱም፡፡

## 6. የአቅርቦቱ ዜሮ መጣኔና ከታክስ ነፃ አፈፃፀም

1) የበጐ አድራጐት ድርጅት በአገር ውስጥ በፈፀማቸው እቃዎች ግዢ ላይ የተከፈለ ታክስ ተመላሽ የሚሆነው በታክስ ተመላሽ መመሪያ መሠረት ነው፡፡
2) የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ለበጐ አድራጐት ሥራ እንዲውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸው እቃዎች ባለሥልጣኑ በአዋጁ፣ በደንቡና በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ያደርጋል፡፡
3) ይህ መመሪያ ለግል መገልገያነት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 7. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ጉዳዮች በነበረው መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

## 8. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተላለፉ ሰርኩላሮችና የአሠራር ልማዶች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

## 9. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ --------------------------ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር